# አገር ፤ አለን አገርማ

ከዙዋይ ረዚን፤ ጀኔቫ

እጂግ ያስደስታል የንፋሱ ቃና
አድማስ ሲፈናጠቅ ከመንጋቱ ገና
ጥዋት ወፍ ሲንጫጫ ሳይቀድማት ማለዳ
ኮረዳዋ ስትወርድ ውሃ ልትቀዳ
ወንዙ በፀጥታ ትልሙን ተከትሎ
ምድርን እያራሰ ሲጓዝ ዝም ብሎ
ቀማምሳ ሲበቃት ካንድ የስንዴ አዝመራ
እርግብ ርቃ ስትበር ወደ ሰማይ ጣራ
ግርማ ለብሶ ሲታይ የዳሽን ተራራ
አዛውንቱ ጭጋግ ከደመና ጋራ
ሲዘል ሲንሳፈፍ ነፍሱ ተሰውራ
እንቁራሪት ስትጨህ ከረግረጉ ውስጥ
የሃይቆች ውበት ልብን ሲመስጥ
ጥሩ መስመር ይዘው አእዋፍ ከላይ ሲያልፉ
ሽታው ልብን ሲያጥን ሙጃው ባሕርዛፉ
ጢስ ቡልቅ እያለ ከጎጆ ሰውጣጣ
ከዛፍዛፍ ስትዘል ተደስታ ጦጣ
ፀደይ በጋው አልፎ ክረምቱ ሲመጣ
ፀሐይዋ ስትጠልቅ ጨረቃ ስትወጣ
ሰማያዊው ሰማይ እጅግ ንፁህ ሆኖ
ኮረብታው ገደሉ በኡዳይ ተሸፍኖ
የሕይወት ደስታ የአገር ትርጉሙ
በዚህ ብቻ ቢቆም የመኖር ዓላማ
ምን ጎደለን ሊባል አለን አገርማ !
ነገር ግን፤

ሕፃን ልጅ ሕፃንን ተጭኖ ካላቀሙ
የማያልፍላቸው ሰዎቹ ቢደክሙ
ብትቶውን ለብሶ ለማኝ ባይታይ
ከቅማል የሚያድን ጠፍቶ ገላጋይ
ባይደራበት ኖሮ ቀማኝ አታላይ
ዳኛው ፍርደገምድል ሰላይ አሾክሻኪ
ባይበዛበት ኖሮ አጉል ትርኪምርኪ
አገርና ሕዝቦቿን እንደገል ንብረት
ጥቂቶች በጥጋብ ባይካፈሉት
አውራጃ ቀበሌው ከላይ እስከታቹ
በጋራ እንዳይለማ ባይገቱ ሕዝቦቹ
የክልል ፈጠራ የነገድ ልዩነት
እንደወግ ተቆጥሮ ባይጀነኑበት
ከጨቋኞች መዳፍ ጥሰን እንዳንወጣ
ማነው የበየነብን ይህን መጥፎ ጣጣ!
ራስን መድፋት በዝቶ ጎደለና ወኔ
ገዝቶ ሊሸጠን ነው የማንም ወያኔ!

ከልደቱ አንሥቶ እስከጊዜ ሞቱ
በአረመኔ ዱላ እንዲቀጭ ሕይወቱ
መታሠር መሰደድ መራብ በየወቅቱ
የደርግ ቀይሽብር የወያኔ አፈና
ጨርቅ ጥሎ የሚያሳብድ የፊሺስት ጭቆና
ዝም ብሎ የሚዋኝ በሕይወት አተላ
ከኢትዮጵያዊው በቀር አይገኝም ሌላ!
የውጋዴን ግመል የአድዋን ፍየል
በእበት በበጠጥ አገር ሳይበክል
ልጓም በማጣቱ ወያኔ ፈርጥጦ
ገደል አፋፍ ሳይደርስ አገር አፈናጦ
አሁን ነው መነሣት በሞት ሽረት ቆርጦ
በጊዜ ቢገራ የበረያ ኮርማ
ትኋኑ ቢጠፋ ገጠርም ከተማ
የአንድነት የመብት ደመቅ ያለው ዓርማ
ባይጋረድ ኖሮ በክህደት ጭለማ
ምን ጎደለን ሊባል አለን አገርማ።

---

TPLF and EPLF cannot be reformed,
like apartheid, they should be abolished!